# ሀሳበ ባሕር

## (የዘመን ቁጥር)

በሊቀ ጉባኤ በዕውቀቱ ይልማ

ጊዜን መቁጠር ዘመንን መስፈር የተጀመረው ከሥነ ፍጥረት ጀምሮ ነው። እግዚአብሔር አምላክ አዳምንና ሄዋንን ፈጥሮ በነፍስ ሕያዋን አድርጎ በመንፈስ ቅዱስ አክብሮ ከአንዲት እፀ በለስ በቀር ከፀሐይ በታች ከምድር በላይ ባለው ሁሉ ላይ አሰልጥኖ (ሾሞ) በገነት አኖራቸው። ሁለቱ የመጀመሪያ ሰዎች ያለምንም ችግር ሕጉን ጠብቀው ትዕዛዙን አክብረው ለሰባት ዓመት በገነት ኖረዋል። "በመጀመሪያው ሱባኤ፣ በመጀመሪያው ኢዮቤልዩ አዳምና ሚስት በገነት" ኖሩ ይላል። ኩፋ 4÷14 ከዚህ በኋላ አዳም በጠላት ዲያብስ ክፉ ምክር ተታሎ ሕጉን ጥሶ፣ ትእዛዙን አፍርሶ ከተሳሳተ በኋላ በገነት ተባረረ። እግዚአብሔርም በዚያው እንደተባረረ እንዲቀር ስላልፈለገ በ5500 ዘመን ሰው ሆኜ አድንሀለሁ ወደ ቀደመ ክብርህ እመልስሃለሁ ብሎ ተስፋ ሰጠው። አዳምም ይህን ተሰፋውን ይዞ ለልጆቹ። ልጆቹም ለልጅ ልጆቻቸው ነገሩአቸው። እነሱም ከአባቶቻቸው ተቀብለው እኩሌቹ በፀሐይ፣ እኩሌቹ በጨረቃ፣ ሌሎቹም በከዋክብት እየቆጠሩ መኖር ጀመሩ። በዚህ ሁኔታ የዘመን አቆጣጠር ታሪክ ተጀመረ።

የዘመን አቆጣጠር ታሪክ መነሻ የ5500 ዘመን መፈጸምን ለመድረስ የሚደረግ ወደ ታች የሚቆጠር ሂደት ነበር። ከአዳም ጀምሮ በዚህ ሁኔታ በዚህ ሁኔታ ቢነሳም በዚሁ አልቀጠለም። ምክንያቱም የሰው ዘር በምድር ላይ እየበዛ በሄደ ቁጥር ለቀን፣ መቁጠሪያ ለዘመን መስፈሪያ፣ ለሰው ልጆች መገልገያ ሊሆኑ የተፈጠሩ ፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብትን የሰው ልጆች አምላካቸው አድርገው አመለኳቸው። ነገር ግን ተስፋቸውን ያልረሱ ጥቂት ሕዝቦች ብቻ እግዚአብሔርን የሚያመልኩ ቀሩ።

ስለሆነም የዘመን አቆጣጠር በልዩ ልዩ ሕዝቦች በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ አካሄዶችን በመከተል ሲሰራብ ኖሯል። በመሆኑም ከአዳም እስከ ልደተ ክርስቶስ ያለውን የዘመን አቆጣጠር ከብዙ በጥቂቱ እንደሚከተለው እናቀርባለን።

## ሱባዔ አዳም፡-

አዳም በገነት ሰባት ዓመት ከአንድ ወር ከአስራ ሰባት ቀን በደስታ ከኖረ በኋላ ምክረ ከይሲን ሰምቶ እፀ በለስን በልቶ ከገነት ወጣ፡፡ ከዚህ በኋላ 35 ቀን ሱባዔ ገብቶ ተጨማሪ 3+3=6 ቀን በመንገድ ቆይቶ ከ41 ቀን በኋላ ተስፋ ሰጠው፡፡

## ሀሳበ ሔኖክ፡-

ሄኖክ በቤተ ክርስቲያንም ሆነ በዓለም ታሪክ የመጀመሪያ የሆነውን መጽሐፍ የጻፈ እሱ ነው፡፡ በሐሳብ ሄኖክ መስፈርት መሠረት 35 ዓመት እንደ መሥፈርት ይቆጠራል፡፡ በሌላ አካሄድ ደግሞ ሰባ ሙቶ ዓመትን እንደ አንድ መሥፈርት ይቆጥራል፡፡ በዚህም መሠረት 35ቱ ዓመት እንደ አንድ ሆኖ በ19 ሲባዛ 665 ዓመት ይሆናል፡፡ ይህም ምፅአቱን የዓለምን ፍጻሜ ያመለክተናል፡፡ ነገር ግን ምፅአቱን የዓለምን ፍፃሜ ከባለቤቱ በቀር የሚያውቅ የለም፡፡ (ማቴ 24÷36 )

## ኢዮቤልዮ ዘሙሴ፡-

ሙሴ ሕግን ከእግዚአብሔር የተቀበለ ያኑ ሕግ ለእስራኤል ያስተላለፈ ያስተማረ ነቢይ ነው፡፡ አያይዞም ትንቢት ተናግሯል ሱባዔ ቆጥሯል፡፡ የሙሴ አቆጣጠር በኢዮቤልዮ ነው፡፡ የእርሱ ኢዮቤልዮም ሦስት ነው፡፡ ሦስቱን እስከ አስራ ዘጠኝ ቢወስዱት 3 ሲበዛ በ19=57 ይሆናል፡፡ ይህም እስ 140 ይሄዳል፡፡ 140X57=7980 ይሆናል፡፡

## ቀመረ ዳዊት፡-

ልበ አምላክ ዳዊት ነቢይም ነው፡፡ ምክንያቱም የአምላክ ሰው መሆን ተገልጦለት እነሆ በጨርቅ ተጠቅሎ በጎል ተጥሎ በግዕዝ ሕፃናት ሲያለቅስ ሰማነው ብሎ ተናግሯልና መዝ 131÷5 ልበ አምላክ ዳዊት ከእርሱ በፊት እንደነበሩት ነቢያት ሱባዔም ቆጥሯል፡፡ "ሺህ ዓመት በፊትህ እንዳለፈች እንደ ትናንት ቀን ናት" ብሎ መዝ 89÷4 ይህም ዘመን ሲቆጠር 1140 ዓመት ይሆናል፡፡ ታዲያ ልበ አምላክ ዳዊት ይህን 1140 ዘመን በእግዚአብሔር ዘንድ እንደ አንድ እለት ነው ብሎ ተናገረ በቀመረ ዳዊት መሠረት ይህ 1140 ዓመት የዘመን መስፈሪያ የቀን መቁጠሪያ ነው፡፡ 1140ውን ዓመት እስከ ሰባት ቢወስዱት 7X1140=7980 ዓመት

ይሆናል። እስከዚህ ድረስ ያለው ከአዳም እስከ ልደተ ክርስቶስ የነበሩ ነቢያት ከቀመሩት ቀመር ለመግቢያ ያህል የተወሰነውን ሲሆን በመቀጠል ግን በሐዲስ ኪዳን በ3ኛው መቶ ክ/ዘመን መጀመሪያ አካባቢ ሊቁ የእስክንድርያው ሊቀጳጳስ ዲሜጥሮስ የደረሰውን ባሕረ ሀሳብ በተለይም በ2006 ዓ.ም በዘመነ ማርቆስ የሚውሉ በዓላትና አፅዋማትና ጨምሮ ተዘጋጅቷል።

## <u>በሐዲስ ኪዳን</u>

ስለዘመን አቆጣጠር የጻፉና ያስተማሩ ብዙ ሊቃውንት አሉ። ከነዚህ ሊቃውንት መካከል የእስክንድርያው ሊቀጳጳስ ዲሜጥሮስ አንዱ ነው። የመጀመሪያውን የዘመን አቆጣጠር ከሐዲስ ኪዳን በዓላት እና አፅዋማት ጋር አስማምቶ የመሠረተ እና ባሕረ ሐሳብ የተባለውን መጽሐፍ የደረሰውም ይኸው ቅዱስ ዲሜጥሮስ ነው።

ባሕረ ሀሳብ ማለት በውስጡ እንደ ባሕር ጥልቀት ያላቸው ጉዳዮች ያሉበት የዘመን ቁጥር ማለት ነው። ስለዚህ ባሕረ ሀሳብ ሲባል የዓመታት፣ የወሮች፣ የሳምንታት፣ የዕለታትና፣ የደቂቃዎች ልክ የሚታወቅበት የዘመን መቆጠሪያ፣ መሥፈሪያ ማለት ነው። መርሐ እውርም ይባላል። በዓላትና አፅዋማት የሚውሉበትን ዕለት ወደ ማወቅ መርቶ ያደርሳልና።

ዲሜጥሮስ ማለት መስታወት ማለት ነው። በመስታወት በዓይን ያለ ጉድፍ እንዲታይም እሱም በዓላት አፅዋማትን አጉልቶ አምልቶ ያሳያልና።

ይህም ቅዱስ ዲሜጥሮስ ድግ ታጥቆ እርፍ አርቆ ተክል አጽድቆ ይኖር የነበረ ገበሬ ነበር። ሚስቱም ልዕልተ-ወይን ትባላለች። እናት አባቷ ሙተውባት ከእርሱ ቤተሰቦች ጋር ያደገች ናት። ነገር ግን እርሱም እሷም ሳይፈልጉ አጋብተዋቸዋል። እናት አባቱም ያጎቱን ልጅ ማጋባታቸው ዘመኑ ምዕመናን ያነሱበት አሕዛብ የበዙበት ዘመን ነበርና ለርሱ የምትሆን ሚስት በመታጣቷ ሕንፃ ሃይማኖት ከማፍረስ ሕንፃ ሥጋ ይፍረስ ብለው ዝምድና እያላቸው አጋብተው ሥርዓተ መርዓዊና መርዓት ያደርሱ ብለው ከጫጉላ አስገቡአቸው ነገር ግን ልዕለተ ወይን ወንድሜ አንተም ነገሩን ሽተኸው ነው? አለችው እርሱም የግድ ቢሉኝ ጊዜ ነው እንጂ ነገሩንስ እንዳልሸው እግዚአብሔር ያውቃል። አሁንም ተለያየን እንደሆነ አንችንም እኔንም ለሌላ ያጋቡናልና በአንድ ላይ ንፅሕ ጠብቀን መኖር እንችላለን ተባብለው በአንድ አልጋ እየተኙ አንድ ልብስ እየለበሱ 48 ዘመን በንፅሕና ኑረዋል። ይኸውም እንዲታወቅ መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል ግራ ክንፉን ለሷ ቀኝ ክንፉን ለሱ አልብሷቸው ያድር ነበር።

ከዕለታት በአንድ ቀን ቅዱስ ዲሜጥሮስ ከአትክልት ቦታ ገብቶ ያለጊዜው ያፈራ የወይን ዘለላ አግኝቶ ወስዶ ሰልዕልተ ወይን ስጣት እርሷም ይህንስ ወስደህ ለሊቀጳጳሱ ሰጥተህ በረከት ተቀበልበት ብላ በንፁሕ ሙዳይ አድርጋ ሰጠችው፡፡

በዘመኑ የነበረው የእስክንድርያው ሊቀጳጳስ ዮልያኖስ ይባል ነበር፡፡ አርጅቶ የሚሞትበት ጊዜ ቀርቦ ነበርና መልአኩ ከአንተ ቀጥሎ የሚሾመው ያለጊዜው ያፈራ የወይን ዘለላ አግኝቶ ወስዶ ለልዕልተ ወይን ሰጣት እርሷም ይህንስ ወስደህ ለሊቀጳጳሱ ሰጥተህ በረከት ተቀበልበት ብላ በንፁሕ ሙዳይ አድርጋ ሰጠችው፡፡ በዘመኑ የነበረው የእስክንድርያው ሊቀጳጳስ ዮልያኖስ ይባል ነበር፡፡ አርጅቶ የሚሞትበት ጊዜ ቀርቦ ነበርና መልአኩ ከአንተ ቀጥሎ የሚሾመው ያለጊዜው ያፈራ የወይን ዘለላ ይዞ የሚመጣ ሰው ነው ብሎ ነግሮት ሰለነበር ዲሜጥሮስ አምጥቶ ሲሰጠው ሕዝቡን ሰብስቦ ከኔ ቀጥሎ የሚሾመው እርሱ ነው ብሎ ነግሮአቸው አርፎአል፡፡

ሕዝቡም እሱን ቀብረው ተመልሰው አባታችን ከኔ ቀጥሎ የሚሾመው እርሱ ነው ብሎናልና ተሾምልን አሉት፡፡

እርሱም ተሹሞ ብዙ መንፈሳዊ ሥራዎችን ከመሥራቱ በተጨማሪ የሕዝቡ ኃጢአት እየተገለፀለት አንተ በቅተሃል ቁረብ አንተ አልበቃህም አትቁረብ እያለ የሚከለክላቸው ሆነ፡፡ ሕዝቡም ተቆጥተው ያጉረመርሙ ጀመር፡፡ በዚህ ጊዜ መልአኩ ተገልጦ ሕዝቡ በሃሜት እየተጎዱ ነውና በአንተና በሚስትህ መሀከል ያለውን ነገር ግለፅላቸው አለው፡፡ እሳት አስነድዶ ሚስቱን ከመቅዋመ አንስ አስጠርቶ ፍሙን በእጁ እየዘገነ (እያፈሰ) ወደ ሚስቱ ልብስ እየጨመረ ሄደሽ ለሕዝቡ አሣይ አላት እሷም ፍሙን (እሳቱን) በልብሷ ይዛ እሳቱ ልብሷን እየዞረች ለሕዝቡ አሣይታለች፡፡ ከዚህ በኋላ ሕዝቡ አባታች በከንቱ አምተንሃልና ይቅር በለን አሉት፡፡ እርሱም ይፍታህ፣ ይኀድግ፣ ያንፅሕ ወይቀድስ ብሎ ናዝዞአቸዋል ኑዛዜ የተጀመረው ከዚያ ወዲህ ነው፡፡

የቀድሞ ሰዎች አቢይ ጾምን የጥምቀት ማግሥት ይጀምሩ ነበር፡፡ ሕማማቱንም አዘግይተው (አቆይተው) በመጋቢት ያደረጉ ነበር፡፡ በዚህ የተነሳ የዓቢይ ጾም የጥምቀትን ሳኒታ መነሻ አድርጎ ስለሚጀመር ሰኞን፣ ደብረዘይት፣ ሆሣዕና፣ ትንሣኤ፣ጰራቅሊጦስ እሁድን ሳይጠብቁ ይውሉ ነበር፡፡

## በዚህም ቅዱስ ዲሜጥሮስ፦

- ጾመ ነነዌ፣ ዓቢይም ጾመ ሐዋርያት ------------------------------------------ከሰኞ
- ደብረ ዘይት፣ ሆሣዕና፣ ትንሣኤ፣ ጰራ ቅሊጦስ ------------------------------ከእሁድ
- ርክበ ካህናት፣ ጾመ ድህነት -------------------------------------------------------ከረቡዕ
- ስቅለት --------------------------------------------------------------------------------ከዓርብ
- ዕርገት --------------------------------------------------------------------------------ከሐሙስ

ባይወጡ? እያለ ሲመኝ ይኖር ነበር። መልአኩ ተገልጦ ነገር በማሰብ ብቻ ይሆናልን ሱባዔ ገብተህ ይገለፅልሃል አለው። ሱባዔ በገባ ጊዜ መላኩ መጥቶ ከመአልቱ ሰባት ሱባዔ ከሌሊቱ ሃያ ሦስት ሱባዔ ገብተህ ይገለጽልሃል። ይህን በ30 በ30 ገድፈህ በተረፈው ታገኘዋለህ ብሎታል። በዚህም መሠረት የመዓልቱ 7X7=49 ይህ በ30 ሲገድፉ 49-30=19 ይቀራል። ይህ 19 የጥንተ መጥምቅ ተባለ። የሌሊቱ 23ቱን አንድ እያለ 7 ጊዜ ይሰገድ ነበር። 23X7= 161 ይን 161 በአምስት 30 ብንገድፈው 161-5X30= 11 ይተርፋል ይህን አበቅቴ ብለው ብሎታል ይህን ቢደምሩት 30 ይሆናል። ይህን አዘጋጅቶ ጽፎ ለ4ቱ ሊቃነጳጳሳት ቢልክላቸው እነሱም ቀድሞ ሐዋርያት ካስተማሩት ትምህርት ጋት ስለገጠመላቸው ደስ ብሏቸው ተቀብለውታል።

መጥቅዕ ቢያንስ አበቅት ቢበዛ አበቅቴ ቢያስ መጥቅዕ ቢበዛ ከ30 አይበልጥም ከ30 አያንስም።

ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ አሁን እስከ አለንበት ቢቆጠር 7506 ዓ.ም ይሆናል። ለዚህም መቁጠሪያ፣ መሥፈሪያ ሰባት አእዋዳ አሉት።

## እነዚህም

- ዐውደ ዕለት
- ዐውደ ወርኀ
- ዐውደ አበቅቴ
- ዐውደ ዓመት
- ዐውደ ፀሐይ

- አውደ ማኅተም
- አውደ ቀመር

የዘመኑን መጥቅና አበቅቴ ለማወቅ አመተ ዓለሙን ለአብይ ቀመር (532) መሥጠት ነው፡፡

7508÷532= 14 ቀሪ 60

ቀሪውን በሦስት ንዑስ ቀመር (19) መጣል፡፡ (19) 60÷19= 3 ቀሪ 3 ይህ መደብ ይባላል፡፡

አሐደ አእትት ለዘመን ብሎ አንድ ቢቀንሱ 3 ይቀራል፡፡

መባጃ ሐመርን ለማግኘት መጥቅዕና በዐለ መጥዕቅ የዋለበት ዕለት ተውሳክ ተደምሮ የሚገኘው ቁጥር መባጀ ሐመር ይባላል፡፡

በዚህም መሠረት መባጃ ሐመር= መጥቅዕ + በዐለ፣ መጥቅዕ የዋለበበት ተውሳክ፡፡

መጥቅዕ ቢበዛ ከመስከረም ንዛ መጥቅዕ ቢያንስ ጥቅምትን ዳስ እንዲሉ መጥቅዕ ሲበዛ በዓለ መጥቅዕ መስከረም ላይ ይውላል፡፡ መጥቅዕ ቢያንስ በዓለ መጥቅዕ ጥቅምት ላይ ይውላል፡፡ መጥቅዕ በዛ የሚባለው ከ14- በላይ ሲሆን ነው፡፡ አነሰ የሚባለው ደግሞ ከ14 በታች ሲሆን ነው፡፡ በዚህም መሠረት የ2008 ዓ.ም በዘመነ ዮሐንስ መጥቅዕ 30 ከ14 በላይ ስለሆነ መስከረም 30 ላይ ሐሙስ ቀን ይውላል፡፡

መባጃ ሐመር = መጥቅዕ + መጥቅዕ የዋለበት ዕለት ተውሳክ፡፡

የሐሙስ ተውሳክ ሦስት ነው መጥቅዕ 30+ የሐሙስ ተውሳክ 3= 33

33 + 30 = 3 መባጃ ሐመር ወጣ በ2008 ዓ.ም በዘመነ ዮሐንስ

የመባጃ ሐመር አገልግሎት የሚሰጡው ከበዓላትና አጽዋማት ተውሳክ ጋር እየተደመረ በዓላ በዕዋማት ማስገኘት ነው፡፡

ከጾመ ነነዌ ውጪ ያሉ አጽዋማትና በዓላት ሁሉም ተውሳክ አላቸው ጾመ ነነዌ ግን ተውሳክ የለውም የሚያገኘው (የሚወጣው) በመባጀ ሐመር ነው፡፡ መጥቅዕ ከዕለት ተውሳክ

ጋር ተደምሮ ከ30 ከበለጠ ጾመ ነነዌ በየካቲት ትውላለች ብለናል፡፡ በመሆኑም የ2006 ዓ.ም መጥቅዕ 30+ የዕለተ ተውሳክ 3

= 33

30 - 30 = 3 መባጀ ሐመር ወጣ በ2006 ዓ/ም በዘመነ ማርቆስ

በዓለ መጥቅዕ ከመስከረም ላይ ሲውል ጾመ ነነዌ በጥር በዓለ መጥቅዕ ከጥቅምት ላይ ሲውል ጾመ ነነዌ በየካቲት ይውላል፡፡

በመሆኑም በ2008 ዓ.ም ፆመ ነነዌን ለማግኘት 3 መባጀ ሐመር +30 መጥቅዕ ተደምሮ ከ30 በላይ በመሆኑ ጾመ ነነዌ በየካቲት ነው የሚውለው በ2008 ዓ/ም በዘመነ ዮሐንስ የካቲት በጥቅምት ማግስት (ሳኒታ) ማክሰኞ ይብታል፡፡

ማክሰኞ ለማክሰኞ 8 ማክሰኞ ለማክሰኞ 15 አንድ ታግሶ ሰኞ 14 የካቲት በገባ በ14 ፆመ ነነዌ ትውላለች፡፡

የአጽዋማት እና በዓላት ተውሳክ

## <u>አፅዋማትና በዓላት ተውሳክ</u>

የዐቢይ ጾም ------------------------------------------------------------------------14

የደብረ ዘይት ----------------------------------------------------------------------11

የሆሳዕና -------------------------------------------------------------------------2

የስቅለት -------------------------------------------------------------------------7

የትንሣኤ ------------------------------------------------------------------------9

የርክበ ካህናት -----------------------------------------------------------------3

የዕርገት ---------------------------------------------------------------------18

የጰራቅሊጦስ -------------------------------------------------------------28

የጾመ ሐዋርያት ------------------------------------------------------------29

የጾመ ድኅነት ----------------------------------------------------------------1

## ዐቢይ ጾም፡-

በ2008 ዓ.ም ዐቢይ ጾም የሚውልበትን ዕለት ለማግኘት የዐቢይ ጾም ተውሳክ 14+ መባጃ ሐመር 14= 28 የካቲት በባተ (በገባ) በ17 ዐቢይ ጾም ይውላል፡፡

## ደብረ ዘይት፡-

በ2006 ዓ.ም ደብረ ዘይት የሚውልበትን ዕለት ለማግኘት የደብረ ዘይት ተውሳክ 11+ መባጃ ሐመር 14 =25 መጋቢት በባተ በ25 (መጋቢት 25 ቀን) ደብረዘይት ይውላል፡፡

## ሆሣዕና፡-

በ2006 ዓ.ም ሆሣዕና የሚውልበትን ዕለት ለማኘት የሆሣዕና ተውሳክ 2+14= 16 ሚያዝያ በባተ በ16 (ሚያዝያ 16 ቀን ) ሆሣዕና ይውላል፡፡

## ስቅለት፡-

በ2008 ዓ.ም ስቅለት የሚውልበትን ዕለት ለማግኘት የስቅለት ተውሳክ 7+14 መባጃ ሐመር= 21 ሚያዝያ በባተ በ21 (ሚያዝያ 21 ቀን) ስቅለት ይውላል፡፡

## ትንሣኤ

በ2008 ዓ.ም የትንሣኤ ተውሳክ 9+14 =23 ሚያዝያ በባተ በ23 (ሚያዝያ 2) ትንሣኤ ይውላል፡፡

## ርክበ ካህናት፡-

በ2008 ዓ.ም ርክበ ካህናት የሚውልበትን ዕለት ለማግኘት (ለማወቅ) የርክበ ካህናት ተውሳክ 3+14 መባጃ ሐመር = 17 ግንቦት በባተ በ17 (ግንቦት 17 ቀን) ርክበ ካህናት ይውላል፡፡

## ዕርገት፡-

በ2008 ዓ.ም ዕርገት የሚውልበትን ዕለት ለማግኘት (ለማወቅ) የዕርገት ተውሳክ 18+3 መባጀ ሐመር = 21

ግንቦተ በባተ በ21 (ግንቦት 21 ቀን) ዕርገት ይውላል፡፡

## ጰራቅሊጦስ፡-

በ2008 ዓ.ም ጰራቅሊጦስ የሚውልበትን ዕለት ለማግኘት (ለማወቅ) የጰራቅሊጦስ ተውሳክ 28+14 መባጀ ሐመር 42- 30 =12

(ሰኔ 12 ቀን) ጰራቅሊጦስ ይውላል፡፡

## ጾመ ሐዋርያት፡-

በ2008 ጾመ ሐዋርያት የሚውልበትን ዕለት ለማግኘት (ለማወቅ) የጾመ ሐዋርያተ ተውሳክ 29+14 መባጀ ሐመር= 43 -30 =13 ሰኔ በባተ በ13

ሰኔ 13 ቀን ጾመ ሐዋርያት ይውላል፡፡

## ጾመ ድኅነት፡-

በ2008 ዓ.ም ጾመ ድኅነት የሚውልበትን ዕለት ለማግኘት የጾመ ድኅነት ተውሳክ 1+14 መባጀ ሐመር = 15

በ4 (ሰኔ 15 ቀን) ጾመ ጽኅነት ይውላል፡፡

በ2008 ዓ.ም በዘመነ ማርቆስ የሚውሉ በዓላት አፅዋማትና የሚውሉባቸው ዕለቶች

ጾመ ነቢያት ------------------------------------------------------------------------ሕዳር 15

ጾመ ነነዌ ---------------------------------------------------------------------------የካቲት 14

ዐቢይ ጾም -------------------------------------------------------------------------የካቲት 28

ደብረ ዘይት ------------------------------------------------------------------------መጋቢት 25

ሆሣዕና -------------------------------------------------------------------------------ሚያዝያ 16

ስቅለት -------------------------------------------------------------------------------ሚያዝያ 21

ትንሣኤ ------------------------------------------------------------------------------ሚያዝያ 23

ርክበ ካህናት -----------------------------------------------------------------------ግንቦት 17

ዕርገት -------------------------------------------------------------------------------ሰኔ 2

ጰራቅሊጦስ ----------------------------------------------------------------------ሰኔ 12

ጾመ ሐዋርያት ------------------------------------------------------------------ ሰኔ 13

ጾመ ድኅነት -----------------------------------------------------------------------ሰኔ 15

ጾመ ፍልሰታ ----------------------------------------------------------------------ነሐሴ 1

እነዚህ ከዚህ በላይ የቀረቡ በ2008 ዓ.ም በዘመነ ዮሐንስ ያሉ በዓላት አጽዋማት የሚውሉባቸው ዕለታት ሲሆኑ በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጭ ያለ ማንኛውም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታይ የሆነ ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን ጠብቆ በዓላትን ለማክበር አፅዋማትን ለመጾም ይጠቅማል ብለን ተስፋ አደርጋለሁ።

ወስብሐተ ለእግዚአብሔር